በእውነቱ፡ አንተ ሰጪው፡ ይቅር ባዩ፡ ምንጊዜም ለጋሱ ነህ:: በእርግጥም፡ አንተ መሐሪው፡ ሩኅሩኁ ነህ::

58

እርሱ አምላክ ነው!

አቤቱ፡ አንተ እጅግ ተወዳጁ የሆንክ ጌታ አምላኬ ሆይ! እነዚህ፡ ድምጽህን የሰሙ፡ ለቃልህ ጆሮዎቻቸውን ያቀኑ፡ ወደ ጥሪህም ያዳመጡ አገልጋዮችህ ናቸው:: በአንተ አምነዋል ፡ የአንተን ድንቅ ሥራዎች አይተዋል፡ የማስረጃህን ትክክለኝነት ተቀብለዋል፡ ስለማረጋገጫህም መሥክረዋል:: በመንገዶችህም ተራምደዋል፡ መርሖህን ተከትለዋል፡ የአንተን ምሥጢራት ተረድተዋል፡ የመጽሐፍህን ድብቅ ይዘት፡ የብሩናህን ጥቅሶች ፡ የመልእክቶችህንና የጽላቶችህንም አስደሳች ዜናዎች ተገንዝበዋል:: በልብስህ ጠርዝ ላይ ተንጠላጥለዋል፡ የብርሃንህንና የታላቅነትህንም ካባ አጥብቀው ይዘዋል:: እርምጃዎቻቸው በቃል-ኪዳንህ መንገድ ተጠናክረዋል፡ ልቦቻቸውም ለአዲሱ ሥርዓትህ ጽኑዎች ሆነዋል:: ጌታ ሆይ! የመለኮታዊ መስብህን ነበልባል በልቦቻቸው ውስጥ አቀጣጥል፡ የፍቅርና የማስተዋል ወፍም ከልቦቻቸው ውስጥ እንድትዘምር ፈቃድህ ይሁን፡ አሳማኝ ምልክቶች፡ እንጸባራቂ ሰንደቅ ዓላማዎች፡ እንደ ቃልህም ፍጹማን እንዲሆኑ አድርጋቸው:: በእነርሱ አማካይነት እምነትህ እንዲከበር፡ የአንተ ዓርማዎች እንዲዘረጉ ፡ ድንቅ ሥራዎችህም በስፋትና በጥልቀት እንዲሰራጩ፡



ቃልህም ድል እንዲነሳ አድርግ፥ የተወዳጆችህንም ወገቦች አበርታ:: ስምህን እንዲያወድሱ አንደበቶቻቸውን አፍታታ፤ የአንተንም ቅዱስ ፈቃድና ፍላጎት ለመፈጸም እንዲችሉ አነቃቃቸው:: ፊቶቻቸውን በቅዱስነት መንግሥትህ ውስጥ አብራ፤ እምነትህ ድልን እንዲጎናጸፍ ለማድረግ እንዲነሡ በመርዳት ደስታቸውን ፍጹም አድርግላቸው::

ጌታ ሆይ! እኛ ደካሞች ነን፥ የቅዱስነትህን መዓዛዎች ለማሰራጨት እንድንችል አበርታን፤ ምስኪኖች ነን፥ በመለኮታዊ አንድነትህ ግምጃ-ቤቶች ውስጥ ከሚገኙት ሀብቶችህ አበልጽገን፤ የተራቆትን ነን፥ የጸጋህን ካባ አልብሰን፤ ኃጢአተኞች ነን፥ ኃጢአታችንን በጸጋህ ፥ በችሮታህና በይቅር-ባይነትህ ይቅር በለን:: በእውነቱ፥ አንተ ረዳቱ፥ አጋዡ፥ ጸጋ የተመላው፥ ኃያሉ፥ ኃይል- የተመላው ነህና::

የእርሱ፥ የንፁዱ ክብር በእነዚያ ጥብቅና ጽኑዎች በሆኑት ላይ ይረፍ::

መንፈሳዊ ባሕርያትን ለማዳበር።

59

በል፡ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ራሴን በፍትሕ ዘውድ፡ አክሊሌንም በትክክለኛነት ጌጥ አጎናጽፈው። አንተ በእውነቱ የስጦታዎችና የበረከቶች ባለቤት ነህና።

60

አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ውበትህ ሕብስቴ፡ የአንተ ቅርበት ብርሃንም ጽዋዬ፡ የአንተም ፍላጎት ተስፋዬ፡ አንተን ማወደስም ሥራዬ፡ አንተን ማስታወስም ባልደረባዬ፡ የአንተ ሉዓላዊነትም እርዳታዬ፡ የአንተ መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቤታዬ፡ ልክ በማርዶሽ እንደተከለለ ከአንተ ከተዘጉት ሰዎች ገደቦች በላይ ከፍ ያደረግኸው መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቤቴ እንዲሆንልኝ ፈቃድህ ይሁን።

በእውነቱ፡ አንተ የሥልጣን፡ የብርታትና የክብር አምላክ ነህና።

61

አምላኬ ሆይ፡ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፡ አለኝታዬ ሆይ፡ የተረጋጋ ኅሊናዬንም በውስጤ አድስ! ከሁሉም በላይ ተወዳጁ ሆይ፡ በኃይል መንፈስ ከእምነትህ ጋር አቁራኘኝ፡ የልቤ ዓላማ ሆይ፡ በክብርህም ብርሃን መንገድህን ግለጽልኝ። የሕይወቴ ምንጭ ሆይ፡ ፍጹም



በላቀው ኃያልነትህ ሥልጣን ወደ ቅድስናህ ሰማይ ከፍ አድርገኝ። አንተ አምላኬ የሆንክ ሆይ፡ በዘለዓለማዊነትህም ልዝብ ነፋስ ሐሴትን ስጠኝ! ባልደረባዬ ሆይ፡ ዘለዓለማዊ የዜማህ ቃናዎች ሰላምን ያውርዱልኝ፡ ጌታዬ ሆይ ፡ የጥንታዊ ገጽህ በረከቶችም ከአንተ በስተቀር ከሌላው ነገር ሁሉ ይጠብቁኝ። አቤቱ አንተ የግልጽ ፍጹም ግልጽ፡ የሥውር ፍጹም ሥውር የሆንክ ሆይ፡ የማይበላሸው የመለኮታዊ ሕላዌህ ግልጸት የምሥራች ሐሴትን ያምጣልኝ።

62

አምላክ ሆይ፡ ለሰው ዘር ላሳየኸው ፍቅር ክብር ላንተ ይሁን! አቤቱ አንተ ሕይወታችንና ብርሃናችን የሆንክ ሆይ፡ አገልጋዮችህን በመንገድህ ምራቸው፡ በአንተም እንድንበለጽግ አድርገን፡ ከአንተም በስተቀር ከሌላው ነገር ሁሉ አንጻን።

አምላክ ሆይ፡ አንተን እንጂ ሌላውን ነገር እንዳናይ ስለአንድነትህ አስተምረን፡ ስለ አንድዬነትህም ግንዛቤን ስጠን። አንተ መሐሪውና ጸጋ ሰጪው ነህና።

አምላክ ሆይ፡ የአንተን በስተቀር የእያንዳንዱን ሌላ ነገር ሃሳብ እንዲያጋይ በተወዳጆችህ ልቦች የፍቅርህን እሳት አቀጣጥል።

አምላክ ሆይ፡ ከእምቅድመ ዓለም የነበርክ፡ እስከ ዘለዓለምም የምትኖር መሆንህንና ከአንተም በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እንገነዘብ ዘንድ

የተከበረ ዘለዓለማዊነትህን ግለጽልን፡፡ በእውነት በአንተ ምቾትንና ጥንካሬን እናገኛለን፡፡

63

እነዚያን ከትክክለኛ መንገድ ወደ ስሕተት መንገድ የተመሩትን ትክክለኞችና የማያዳሉ እንዲሆኑ፥ ደንታቢስ የሆኑበትን እንዲገነዘቡ በጸጋው እንዲረዳቸው እግዚአብሔርን እንለምነዋለን፡፡ እርሱ በእውነቱ፥ ፍጹም ጸጋ የተመላው፥ ከሁሉም በላይ ለጋሱ ነው፡፡ ጌታዬ ሆይ፥ አገልጋዮችህን ከጸጋህ በር አትከልክላቸው፥ ከቅርበትህም መንበር አታርቃቸው፡፡ የአጉል እምነትን ጭጋግ እንዲያስወግዱ፥ የከንቱ አስተሳሰብንና የከንቱ ምኞትን ግርዶሽ ቀዳደው እንዲጥሉ በጸጋህ እርዳቸው፡፡ አንተ በእውነቱ ሁሉ ነገር ያለው፥ ከሁሉ በላይ ከፍተኛው ነህ፡፡ ከአንተ ከፍጹም ኀያሉ፥ ጸጋ ከተመላው በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡

64

(በሴት የሚደረግ)

አቤቱ ጌታዬ ሆይ! እኔ ከአንተ ሴት አገልጋዮች መካከል አንዷ ነኝ፡፡ ፊቴን ጸጋ ወደተመላበት ችሮታዎችህ ክልልና ወደሚመለከው የክብርህ መቅደስ መልሼአለሁ፡፡ ውበትህን በማሰላሰል እንድደሰት ፥ ከፍጡሮችህ መካከል ከማንኛውም ጋር በአጉል ቁራኛነት ከመጣበቅ ሁሉ እንድላቀቅ ፥ በእያንዳንዷም ቅጽበት *"የዓለማት ጌታ የሆነው አምላክ የተወደሰ ይሁን"* በማለት እንዳውጅ፥ የአንተ ካልሆነው



ነገር ሁሉ አንጻኝ፣ አንተንም እንዳፈቅርና ፍላጎትህን ለማሟላት እንድችል አበርታኝ፡፡

አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ውበትህ ሕብስቴ፥ የአንተ ቅርበት ብርሃንም ጽዋዬ፥ የአንተም ፍላጎት ተስፋዬ፥ አንተን ማወደስም ሥራዬ፥ አንተን ማስታወስም ባልደረባዬ፥ የአንተ ሉዓላዊነትም እርዳታዬ፥ የአንተ መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቦታዬ፥ ልክ በግርዶሽ እንደተከለሉ ከአንተ ከተዘጉት ሰዎች ገደቦች በላይ ከፍ ያደረግኸው መኖሪያ ሥፍራም መኖሪያ ቤቴ እንዲሆንልኝ ፈቃድህ ይሁን፡፡

በእውነቱ፥ አንተ የሥልጣን፥ የብርታትና የክብር አምላክ ነህና፡፡

65

አቤቱ አንተ የአገሮች ፈጣሪና የዘለዓለም ንጉሥ የሆንከው ሆይ፥ ሴት አገልጋዮችህን በአንተ የክብረ ንጽህና መቅደስ ውስጥ እንድትጠብቃቸው፡ እነዚያን ለቀናትህ ብቁ ያልሆኑትን ዓይነት አድራጎቶቻቸውንም ይቅር እንድትልላቸው እማጸንሃለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ፥ ጥርጣሬዎችንና ከንቱ አስተሳሰቦችን ከእነርሱ አንጻ፥ አቤቱ አንተ የስሞች ሁሉ ጌታና የንግግር ምንጭ የሆንከው ሆይ፡ ከአንተ ጋር ላላቸው ዝምድናዎቻቸው ተገቢ ካልሆኑት ከማናቸውም ነገሮች ቀድሳቸው፡፡ አንተ የመላው ፍጥረት ግዛት በመዳፉ ውስጥ ያለው ነህና፡፡

ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፡ ከሁሉም በላይ ከተከበረው፡ ከንዑዱ፡ በገዛ ራሱ ከሚኖረው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡

66

አምላክ ሆይ! መንፈሴን አድስልኝ፡ አስደስትልኝም። ልቤን አንፃልኝ። አዕምሮዬን አብራልኝ። ጉዳዮቼን ሁሉ በአንተ ላይ ጥዬአለሁ። አንተ መሪዬና መሸሻዬ ነህ። ከእንግዲህ ወዲያ የተከፋሁና ኃዘንተኛ አልሆንም፥ ደስተኛና በሐሴት የተመላሁ እሆናለሁ። አምላክ ሆይ ፥ ከእንግዲህ ወዲያ በሥጋት ውስጥ አልዋኝም፥ ችግርም እንዲያስጨንቀኝ መንገድ አልሰጥም። ደስ በማያሰኝ የሕይወት ነገር ውስጥ አልኖርም። አምላክ ሆይ! አንተ ከራሴ ይልቅ ለኔ ትራራልኛለህ። ጌታ ሆይ፡ ራሴን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ።

67

አቤቱ፡ አንተ ሩኅሩኅ አምላክ ሆይ፥ አንተ ከራሴ ይልቅ ትራራልኛለህ። ፍቅርህም በጣም ከፍተኛና እምቅድመ ዓለማዊ ነው። የአንተን በረከት ባስታወስኩ ጊዜ ደስተኛና ባለተስፋ ነኝ።

በምበሳጭበት ጊዜ የልብና የነፍስ ዕረፍት አገኛለሁ። በምታመምበት ጊዜ ዘለዓለማዊ ጤንነት ይኖረኛል። እምነቱን በማጓድልበት ጊዜ ታማኝ እሆናለሁ። ተስፋ ቢስ በምሆንበት ጊዜ ተስፋ ይኖረኛል።

አቤቱ፡ አንተ የመንግሥቱ፡ ጌታ ሆይ! ልቤን ደስ አሰኝልኝ። ደካማ መንፈሴን አበርታልኝ ። የቆረቆዙ ጅማቶቼንም አጠንክርልኝ፣ ዓይኖቼንም አብራልኝ፣ የመንግሥትህን ዜማ እንድሰማና ዘለዓለማዊ ተድላና



ደስታ እንዳገኝ ጆሮዎቼን አንቃልኝ። በእውነቱ፥ አንተ ቸሩ፡ ሰጪውና ሩኅሩኅ ነህና።

68

አቤቱ፡ የተከበርክ ጌታዬ ሆይ! አንተን ለማገልገልና ቃልህንም ለማስተማር እበቃ ዘንድ፥ ከማንኛውም ሕገወጥ ዝንባሌ እንድታቀብ፥ ማንኛውንም አመጸኛ ስሜት እንዳሸንፍ፥ የምግባሬንም ዓላማ እንዳነፃ፥ ምንም ትንኮሳ በማይረብሸው ትሑትነት፡ ምንም ስቃይ በማይበግረው ትዕግሥት፥ ምንም ራስ ወዳድነት በማያናውጠው ሐቀኛነት. እንድኖር እርዳኝ።

69

አቤቱ፡ አንተ ሩኅሩኅ አምላክ ሆይ! እንደ መስታወት በፍቅርህ ብርሃን የሚያንጸባርቅ ልብ ፍጠርልኝ። ይህን ዓለም በመንፈሳዊ የጸጋ ኅርፎች አማካይነት ወደ ጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ለመለወጥ የሚያስችሉኝን አስተሳሰቦች ለግሰኝ።

አንተ ሩኅሩኅ ፥ መሐሪው ነህና! አንተ ታላቁ ቸር አምላክ ነህና።

ለሰው ዘር፡፡

70

የማመልክህና የማወድስህ አምላኬ ሆይ! ስለአንድነትህና ስለ አንድዬነትህ እመሠክራለሁ፡ በፊት ለሰጠኸኝና አሁንም ለምትሰጠኝ ስጦታህ አመሰግንሃለሁ፡፡ አንተ የምሕረቱ የሚያጥለቀልቁ ዶፎች በታላላቆቹም በታናናሾቹም ላይ ያለልዩነት የዘነቡት፥ የጸጋውም ደማቅ ብርሃኖች በታዛገርችም በአመጸኞችም ላይ ያበሩት ፍጹም ቸር ጌታ ነህ፡፡

አቤቱ አንተ የምሕረት ህልውና በእርሱ በር ደጃፍ ፊት የሰገደው፥በእርሱም እምነት መንበር ዙሪያ፥ ፍቅራዊ ደግነት ከሁሉ በላቀ ውስጣዊ መንፈሱ የከበበው የምሕረት አምላክ ሆይ፥ የሰው-ዘር ዓለም መገለጫዎች በሆኑት ሁሉ ላይ ምሕረት እንዲኖርህ፥ በቀናትህም ከጸጋህ ዝናቦች እንዳትነፍጋቸው፥ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ጸጋህን እየተማለድን፥ የአሁኑንም ጊዜ ችሮታህን እየለመንን እንማጸንሃለን፡፡

ሁሉም ድሆችና ችግረኞች ናቸው፥ አንተ ግን በእውነቱ፥ ሁሉ ያለው፡ ሁሉን አስገባሪው፡ፍጹም ኃይል የተመላው ነህ፡፡

71

ጌታ ሆይ! ማንም የተፈጠረ ሕያው ከመልካም ፈቃድህ ክልሎች ውጪ እንዳይቀር፥ ሁሉንም የምድር ሕዝቦች ወደ እምነትህ ገነት የመግባትን ጸጋ ለማግኘት አስችላቸው፡፡



አንተ ሊታወስ ከማይቻል ጊዜ ጀምሮ የሚያስደስትህን ለማድረግ ችሎታ ያለህ፥ ከምትሻውም ከማንኛውም ነገር በላይ ሆነህ ኖረሃል፡፡

72

አቤቱ አንተ ሩኅሩኅ አምላክ ሆይ! የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ምንጭ ፈጠርክ፡፡ ሁሉም አንድ ቤተሰብ ይሆኑ ዘንድ አዘዝህ፡፡ በቅዱስ ቅርበትህ ሁሉም አገልጋዮችህ ናቸው፤ የሰው ልጆችም ሁሉ በመንበርህ ሥር ይጠለላሉ፤ ሁሉም በበረከትህ ማዕድ ዙሪያ ተሰብስበዋል፡፡ ሁሉም በአምላካዊ ጥበቃህ ብርሃን አንጸባርቀዋል፡፡

አምላክ ሆይ፥ አንተ ለሁሉም ደግ ነህ፥ ለሁሉም አስፈላጊውን አድለሃል፥ ለሁሉም መጠለያ ትሆናለህ፤ ለሁሉም ሕይወት ትሰጣለህ፥ ለእያንዳንዱም ተሰጥኦንና ችሎታን ሰጥተሃል፤ ሁሉም በምሕረትህ ውቅያኖስ ውስጥ ሰጥመዋል፡፡

አቤቱ ቸር አምላክ ሆይ! ሁሉን አስተባብር፡፡ የሰው ልጆች አንድ ቤተሰብ እንዲሆኑና መላዋን ምድር እንደ አንድ መኖሪያቸው እንዲያደርጉአት፥ ሃይማኖቶች እንዲስማሙ አድርግ፥ ሀገሮችንም አንድ አድርጋቸው፡፡ ሁሉም በፍጹም አንድነትና ስምምነት እንዲኖሩ ፈቃድህ ይሁን፡፡

አምላክ ሆይ! የሰውን ዘር አንድነት ሰንደቅ ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርገው፡፡

አምላክ ሆይ! ታላቁን ሰላም መሥርት፡፡

አምላኬ ሆይ! ልቦችን በጽኑ አስተባብር፡፡

አቤቱ፥ ቸር አባት የሆንክ አምላክ ሆይ! በፍቅርህ መዓዛ ልቦቻችንን ደስ አሰኘልን። በመርሖህም ፋና ዓይኖቻችንን አብራልን። በቃልህ ዜማ ጆሮዎቻችንን አስደስትልን፤ በአምላካዊ ጥበቃህ ምሽግ ውስጥ ሁላችንንም ጠልለን።

አንተ ኃያሉና ብርቱው ነህ፤ አንተ ይቅር-ባዩ ነህ፥ አንተ የሰውን ልጆች ጥፋት የማይከታተለው ነህና።

73

አቤቱ፥ አንተ ሩኅሩኅ፥ ቸርና ሁሉን የምትችል ጌታ ሆይ! እኛ በአምላካዊ ጥበቃህ ሥር ተጠልለን የምንገኝ አገልጋዮችህ ነን። የፍቅር አንጻርህን አሳርፍብን። ለዓይኖቻችን ብርሃንን፥ ለጆሮቻችን መስማትን፥ ለልቦቻችን ማስተዋልንና ፍቅርን ስጥልን። በምሥራች ዜናህ ነፍሶቻችንን አስደስትልን። ጌታ ሆይ! የመንግሥትህን መንገድ አሳየን፤ በመንፈስ ቅዱስህም እስትንፋስ በሁላችን ነፍስ ዝራብን። ዘለዓለማዊ ሕይወትን ስጠን፤ የማይሻረውንም ክብር አጎናጽፈን። የሰውን ልጆች አንድ አድርጋቸው፥ የሰውንም ዘር ዓለም . አብራ። መንገድህን እንድንከተል፥ ፈቃድህን እንድንናፍቅ፥ የመንግሥትህንም ምሥጢር እንድንሻ አድርገን። አምላክ ሆይ! አስተባብረን፤ ልቦቻችንንም ከቶ ከማይፈርሰው ኅብረትህ ጋር አስተሳስርልን። በእውነቱ፥ አንተ ሰጪው ነህ፥ አንተ ሩኅሩኅ ነህ፥ አንተ ፍጹም ኃያሉ ነህና።



<u>ለጥበቃ</u>

74

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ ስምህ የተወደሰ ይሁን! ወደ አንተ ተመልሰው የአንተን እምነት ለረዱት አገልጋዮችህ ልቦቻቸውን የሚያስደስተውን ከምሕረትህ መንግሥተ ሰማይና ፍቅር ከተመላበት የአንተ የርኅራኄ ደመናዎች እንድታዘንብላቸው፥ ሰዓቱ በደረሰበት፥ ትንሣኤውም በተፈጸመበት፥ ፍርሐትና መንቀጥቀጥም በእነዚያ በሰማይ በሚገኙት ሁሉ፥ በምድር ላይ በሚገኙትም ሁሉ ላይ በወረደበት ስምህ እማጸንሃለሁ።

ጌታ ሆይ፥ ወንድ አገልጋዮችህንና ሴት አገልጋዮችህን ከእውነት የራቁ እምነቶችና የከንቱ አስተሳሰቦች ጦሮች ሊያደርሱባቸው ከሚችሉት አደጋዎች እንድትጠብቃቸው፥ ከጸጋህም እጆች፥ በለዘብታ የሚወርዱትን የዕውቀትህን ውሀዎች መጠጥ እንድትሰጣቸው እለምንሃለሁ።

አንተ በእውነቱ፥ ፍጹም ኃያሉ፥ ከሁሉ በላይ የተከበረው፥ ዘላለም ይቅር-ባዩ፥ ከሁሉም በላይ ለጋሱ ነህና።

75

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! የፍቅርህን ገመድ አጥብቄ በመያዝ፥ ራሴንም ሙሉ በሙሉ ለአንተ እንክብካቤና ለጥበቃህ በመስጠት ከቤቴ ወጥቻለሁ። ተወዳጆችህን ከእነዚያ ከትክክለኛው መንገድ ከራቁትና ከጠማማዎቹ፥ ከእያንዳንዱም አመጸኛ ጨቋኝ፥

ከእያንዳንዱም ከአንተ የራቀ ክፉ አድራጊ በጠበቅህበት ኃይልህ ፡ እኔንም በቸርነትህና በጸጋህ ከማንኛውም አደጋ እንድትጠብቀኝ እማጸንሃለሁ። በሥልጣንህና በኃያልነትህም በደህና ወደቤቴ ለመመለስ አስችለኝ።

በእርግጥ አንተ ፍጹም ኃያሉ፥ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፥ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህና።

76

አምላኬ ሆይ! ማናቸውንም ፈቃዴን ሁሉ አንተ በቅዱስ ጽላትህ ላይ በጻፍከው መሠረት እንድወስን፥ በገዥነትህ ሥልጣን ካዘዝከው ውጭ የሆነውን ምኞት ሁሉ እንዳልመኝ፥ በፈቃድህም ካዘዝከልኝ ዕድል በስተቀር የሌላ ፍላጎት ከቶ እንዳያድርብኝ፥ ግርማው ሰማይንና ምድርን በከበበው ስምህ እለምንሃለሁ።

77

በል፦ እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ከሁሉም በላይ ያረካል፤ በሰማይና በምድር ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያረካ የለም፤ በእውነቱ እርሱ በራሱ አዋቂው፥ ሕይወት ሰጪው፡ ምንም የማይሳነው ነው።

78

ጌታዬ ሆይ! የሁሉን ነገሮች አስቀድሞ የታዘዘ መጠን በእጅህ መዳፍ ውስጥ ይዘሃልና፥ ለእኔና ለእነዚያ ለሚያምኑብህ፥ ያንን በእናት መጽሐፍ ውስጥ እንደሠፈረው፥ በአንተ ግምት ይበልጥ



እንደሚጠቅመን ያሰብከውን እዘዝልን።

መልካም ሥጦታዎችህ፥ በእነዚያ ፍቅርህን በሚወዱት ላይ ያለማቋረጥ ይዘንባሉ፤ የመንግሥተ ሰማያዊ በረከቶችህም ድንቅ ምልክቶች፥ ለእነዚያ መለኮታዊ አንድነትህን ለተቀበሉት በበቂ መጠን ይሰጣሉ። ለእኛ ያዘጋጀህልንን ማንኛውንም ነገር ለጥበቃ ለአንተ እንሰጣለን፤ ዕውቀትህ የሚያቅፈውንም መልካም ነገር ሁሉ እንድትሰጠን እንማጸንሃለን።

ጌታዬ ሆይ፥ ሁሉን አዋቂነትህ ከሚያየው ክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀን፤ ኃይልና ብርታት በአንተ እንጂ በሌላ የለምና፤ ድል አድራጊነትም ከአንተ ዘንድ በቀር ከሌላ አይመጣምና፤ ማዘዙም የአንተ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የፈቀደው ማንኛውም ነገር ሆኗል፤ እርሱ ያልፈቀደውም አይሆንም።

ከሁሉም በላይ በተከበረው፥ በፍጹም ኃያሉ አምላክ በቀር በሌላ ኃይልም ብርታትም የለም።

79

አምላክ ሆይ፥ ክብር ለአንተ ይሁን! አንተ ከሁሉ ነገሮች በፊት የነበርክ፥ ከሁሉ ነገሮች በኋላ የምትኖርና ከሁሉም ነገሮች በኋላም አልፈህ የምትቆይ አምላክ ነህ። አንተ ሁሉን ነገሮች የሚያውቀው፥ በሁሉ ነገሮችም ላይ የላቀ የበላይ የሆነው አምላክ ነህ። አንተ ሁሉን ነገሮች በምሕረት የምትዳስሰው፥ በሁሉ ነገሮችም መካከል የሚፈርደው፥የማየት ኃይሉም ሁሉን ነገሮች የሚያቅፈው አምላክ ነህ። አንተ አምላክ ጌታዬ ነህ፤ አንተ ስለሁኔታዬ ታውቃለህ፤

አንተ ውሳጣዊውንና ውጫዊውን ሕያውነቴን ታያለህ። ለእኔና ለጥሪህ መልስ ለሰጡት አማኞች ይቅር ባይነትህን ስጠን፥ ኃዘን ሊያደርስብኝ ከሚፈልግ ወይም ክፉ ከሚመኝልኝ ከማንኛውም ሰው ጉዳት የሚከላከልልኝ አርኪ ረዳቴ ሁን። በእውነቱ አንተ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ጌታ ነህ። አንተ እያንዳንዱን ሰው ታረካለህ፣ ነገር ግን ማንም ያለ አንተ እርዳታ ራሱን የሚችል ለመሆን አይችልም።

80

*በስመ እግዚአብሔር፡ በሚያርበደብደው ግርማ ጌታ፡ በሁሉን አስገዳጁ!*

የገገርነት ምንጭ በእጁ ውስጥ ያለው ጌታ የተቀደሰ ይሁን። እርሱ፥ "ሁን" ሲል በሚሆነው የትእዛዝ ቃሉ የፈቀደውን ማንኛውንም ነገር ይፈጥራል። የሥልጣን ኃይል ከዚህ በፊት የእርሱ ነበር፥ ለወደፊቱም የእርሱ መሆኑን ይቀጥላል። እርሱ የፈለገውን ማንኛውንም ሰው በትእዛዙ ፍጹም ኃይል ድል አድራጊ ያደርገዋል። እርሱ በእውነቱ ኃይል የተመላው ፥ ፍጹም ኃያሉ ነው። በግልጸትና በፍጥረት ዓለማት በመካከላቸውም በሚገኘው በማንኛውም ውስጥ ክብርና ግርማ ሁሉ የእርሱ ናቸው። በእውነቱ እርሱ ምንም የማይሳነው፥ንዑዱ ነው። ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ እርሱ የማይበገር ኃይል ምንጭ ነበር፥ በዚህም ሁኔታ ለዘለዓለም ይኖራል። እርሱ በእርግጥ የኃያልነትና የሥልጣን ጌታ ነው። በሰማይና በምድር፥ በመካከላቸውም የሚገኙት ዓለማት ሁሉ



የአምላክ ናቸው፡ ሥልጣኑም በሁሉም ነገሮች ላይ የላቀ የበላይ ነው። የምድርና የሰማይ ሀብት ሁሉ፥ በመካከላቸውም የሚገኙት ነገሮች ሁሉ የእርሱ ናቸው፡ ጥበቃውም በሁሉም ነገሮች ላይ ተዘርግቶ ይገኛል። እርሱ የሰማያትና የምድር፥ በመካከላቸውም የሚገኝ የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ነው፥ በእውነቱ እርሱ በሁሉ ነገሮች ላይ ምሥክር ነው። እርሱ በሰማያትና በምድር የሚኖሩትን፥ እንዲሁም በመካከላቸው የሚግኙትን ሁሉ ስለሥራቸው የሚጠይቅ ጌታ ነው፡ በእውነቱ እግዚአብሔር ስለተሠሩት ሥራዎች ለመጠየቅ ፈጣን ነው። እርሱ በሰማያትና በምድር በመካከላቸውም ለሚገኘው ሁሉ የተመደበውን ድርሻ መጠን ይወስናል። በእውነቱ፥ እርሱ የላቀው ጠባቂ ነው። እርሱ የሰማይንና የምድርን በመካከላቸውም የሚገኘውን ነገር ሁሉ ቁልፎች በመዳፉ ውስጥ ይይዛል። እርሱ በገዛ ራሱ ፍላጎት፥ በራሱ ትእዛዝ ሥጦታዎችን ይሰጣል። በእርግጥ ጸጋው ሁሉን ያቅፋል፡ እንዲሁም እርሱ ሁሉን አዋቂው ነው።

በል፦ እግዚአብሔር ለእኔ አርኪዬ ነው፤ እርሱ የሁሉንም ነገሮች ዓለም በመዳፉ ውስጥ የያዘው ነው። በሰማያትና በምድር በመካከላቸውም በሚገኙት የእርሱ ሠራዊት ኃይል ፥ ከአገልጋዮቹ መካከል የፈለገውን ማንኛውንም ሰው ይጠብቃል። በእውነቱ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ይጠብቃል።

ጌታ ሆይ፥ ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ! በፊት ለፊታችንና ከበስተኋላችን፥ ከእራሶቻችን በላይ፥ ከበስተቀኛችን፥ ከበስተግራችን፥ ከእግሮቻችን

በታችና በተጋለጥንበት በእያንዳንዱ ሌላ ጎን በኩል ከሚገኘው ከማንኛውም ነገር ጠብቀን:: በእውነቱ የአንተ ጥበቃ ከሁሉም ነገሮች ላይ አይቋረጥም:: [1]

## 81

ጌታዬ ሆይ! ሕዝቦች ሁሉ በጭንቅና በመከራ÷ በልፋትና በችግር የተከበቡ መሆናችውን አንተ ታውቃለህ:: እያንዳንዱን ሰው ልዩ ልዩ ፈተና ይገጥመዋል÷ የእባብ ንክሻን የመሰለ አደገኛ ችግርም ይደርስበታል::ተከላካይነትና ጠባቂነት ከተመላው ከአንተ ክንፍ በስተቀር ሰው ሌላ መጠጊያና መሸሸ የለውም::

አቤቱ አንተ መሐሪው አምላክ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! ጠባቂነትህን የብረት ልብሴ÷ ክብካቤህን ጋሻዬ ÷ በአንተ አንድነት ደጅ ላይ ትሕትና ማሳየቴን ጠባቂዬ÷ ተከላካይነትህንና መከታነትህን ምሽጌና መኖሪያዬ አድርግልኝ:: ለራሴና ለምኞቴ ቅድሚያ ከመስጠት ጠብቀኝ:: ከማንኛውም ሕመም÷ ፈተና÷ ችግርና ጭንቀት አድነኝ::

በእውነቱ አንተ ጠባቂው÷ ሞግዚቱ÷ በሕይወት የሚያቆየው÷ አርኪው ነህና፤ በእርግጥም አንተ ከሁሉ በላይ መሐሪዎች ከሆኑት ሁሉ በላይ ፍጹም መሐሪው ነህና::

......................

1. የዚህ የጥበቃ ጸሎት የመጀመሪያ ጽሑፍ በባብ በራሱ እጅ: በሰው ቅርጽ በተመሰለ: አምሥት ጫፍ ያለው ኮከብ በሚመስል ቅርጽ የተጻፈ ነው::



## 82

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! ታማኝ አገልጋዮችህን ሁሉ ከእኔነትና ከብርቱ ስሜት ኃጢአት ከልላቸው. በጠባቂው የፍቅራዊ ደግነትህ ዓይን ከማናቸውም ክፋት: ጥላቻና ቅናት ጠብቃቸው: የጥርጣሬ ጦሮች በማይደርሱበት በማይደፈረው የጥበቃህ ምሽግ ውስጥ ከልላቸው: ክብር የተመሉት ምልክቶችህ መገለጫዎች አድርጋቸው: ከመለኮታዊ አንድነትህ ጎሕ በሚፈነጠቁ አንጸባራቂ ጨረሮች ፊቶቻቸውን አብራ: ከቅዱስ መንግሥትህ በተገለጹ ጥቅሶች ልቦቻቸውን አስደስት: ከክብር መንግሥትህ በሚመጣው ሁሉን በሚገዛው ኃይል ክንዳቸውን አበርታ:: አንተ ፍጹም በረከት የተመላው: ጠባቂው: ፍጹም ኃያሉ: ጸጋ የተመላው ነህና::

## 83

አንተ ፊትህን ወደ አምላክ የምታቀና ሆይ! ዓይኖችህን በሁሉም ሌሎች ነገሮች ላይ ጨፍነህ ለንዑዱ አምላክ ዓለም ግለጣቸው:: የምትሻውን ማንኛውንም ነገር ከእርሱ ብቻ ጠይቅ፡ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ከእርሱ ብቻ ፈልግ:: በአንዲት እይታ መቶ ሺህ ተስፋዎችን ይሰጣል: በጨረፍታ እይታም መቶ ሺህ የማይድኑ ደዌዎችን ይፈውሳል: በቅጽበታዊ እይታም በእያንዳንዱ ቁስል ላይ መድኃኒት ያደርጋል: በአንዲት የይሁንታ ምልክትም ልቦችን ከኃዘን ሰንሰለት ነፃ ያወጣል:: የፈለገውን

ያደርጋል፥ ምንስ ምርጫ አለን? ፈቃዱን ይፈጽማል፥ የፈለገውን ነገር ያዛል። ስለዚህ በመታዘዝ መንፈስ ራስህን መድፋትና እምነትህን በፍጹም መሐሪው ጌታ ላይ ማድረግ ይሻልሃል።

84

## እርሱ አምላክ ነው!

ጌታ አምላኬ ሆይ! አቤቱ፡ አንተ የደካሞች ረዳት፥ የድሆች አጋዥ፥ ረዳት የሌላቸውንና ወደ አንተ የተመለሱትን አዳኝ ሆይ!

ወደ አንተ የውበት መንግሥት ተማጣኝ እጆቼን በፍጹም ዝቅተኛነት እዘረጋለሁ፤ በቃለ የውስጣዊ አንደበቴም እንዲህ እያልኩ አንተን እጠራለሁ። እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! አንተን እንዳመልክ እርዳኝ፤ አንተን እንዳገለግል ሽንጦቼን አጠንክርልኝ፤ ለአንተ ባለኝ አገልጋይነቴ ተግባር በጸጋህ እርዳኝ፤ ለአንተ በታዛዥነቴ ጸንቼ እንድቆይ አድርገኝ፤ የቸርነትህንም የተትረፈረፈ ጎርፍ በላዬ አፍስልኝ፤ የፍቅራዊ ደግነትህ ዓይን እይታዎች አቅጣጫቸውን ወደኔ እንዲመልሱ ፈቃድህ ይሁን፤ በይቅር-በይነትህም ውቅይኖስ ውስጥ አስጥመኝ። ለእምነትህ፥ በታማኝነቴ የተደላደልኩ እንድሆን ፍቀድልኝ፤ ከዓለም በፍጹም እንድላቀቅ፥ በፍጹም ፍቅር ፊቴን ወደ አንተ ፊት እንድመልስ፥ በማረጋገጫዎችህና በምሥክሮችህ ኃይል እንድጠናከር፥ ግርማንና ኃይልንም በመጎናጸፍ ከእያንዳንዱ የሰማይና የምድር



አካባቢ ባሻገር እንዳልፍ፥ የተሟላ መተማመንንና እርግጠኝነትን አድለኝ። በእውነቱ አንተ መሐሪው፥ ንዑዱ፥ ቸሩ፥ ሩኅሩኅ ነህና።

ጌታ ሆይ! እነዚህ ፥ የእነዚያ የተባረኩ ነፍሶች፥ የሰማዕታት ልጆች ናቸው። እያንዳንዱን ሥቃይ ተሸክመው ባሳዛኝ ፍትሕ አልባነት ሥር ፍጹም ትዕግሥትን አሳይተዋል። ሁሉንም ምቾትና ብልጽግናን ትተዋል፤ በፍቅርህም መንገድ ለአደገኛ ሥቃይና መከራ በፈቃዳቸው ራሳቸውን ሰጥተዋል፤ በቀና መንገድህ በጽናት በመራመዳቸው አሁንም በማያቋርጥ የከፋ ሥቃይ በሚያሠቃዩአቸው ጠላቶቻቸው እጅ በምርኮኝነት ይገኛሉ። ማንም የሚረዳቸው የለም፥ ማንም የሚወዳጃቸው የለም። ከወራዶችና ከክፉዎች በስተቀር ከእነርሱ ጋር የሚቀላቀልና የሚወያይም የለም።

ጌታ ሆይ! እነዚህ ነፍሶች በዚህ በምድራዊ ሕይወት መራራ ሥቃይን ቀምሰዋል፤ ለገጽታህም አንጸባራቂ ውበት ላላቸው ፍቅር ምልክት እንዲሆንና ወደ አንተም መለኮታዊ መንግሥት ለመድረስ ባላቸው ጉጉት ጨቋኝ ሕዝቦች በእነርሱ ላይ ያወረዱትን ከባድ ውርደት ችለዋል።

ጌታ ሆይ! በመለኮታዊ እርዳታና በፈጣን ድል ጥቅሶች ጆሮዎቻቸውን ሙላ፤ ከእነዚያም አስከፊ ኃይል ካላቸው ሰዎች ጭቆና አድናቸው። የእኩያንን እጆች ግታ፤ ለአንተ ባላቸው ፍቅር በመማረካቸው፥ የቅድስናህ ምሥጢር ባለአደራ በመሆናቸው፥ በደጃፍህ በትሕትና በመቆማቸውና ወደ ከፍተኛው

በእውነቱ፡ አንተ ምንም የማይሳነው፥ በረከት የተመላው ነህና። ከአንተ ከኃያሉ፥ ጸጋ ከተመላው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

## 86

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ አንተ የተከበርክ ነህ! ስለአንተ ለማውሳት በሞከርኩ ቁጥር፥ በከባድ ኃጢአቶቼና በአንተ ላይ በፈጸምኩአቸው አሳዛኝ በደሎቼ እገታለሁ፥ ከጸጋህም ሙሉ በሙሉ ተነፍጌ፥ የአንተን ምስጋና ለማወደስም ፍጹም ኃይል-አልባ ሆኜ እገኛለሁ። ሆኖም፥ በጸጋህ ላይ ያለኝ ታላቅ እምነት፥ በአንተ ላይ ያለኝን ተስፋ ያድስልኛል፥ አንተ ቸርነት በተመላበት ሁኔታ እንደምትለግሰኝ ያለኝ እርግጠኝነትም እንዳወድስህና አንተ ያለህን ነገሮች ሁሉ ከአንተ እንድለምን ያደፋፍረኛል።

አምላኬ ሆይ፥ ልቤ ለክፋት የተጋለጠ ስለሆነ፥ ለራሴ እንዳትተወኝ፥ በስሞችህ ውቅያኖሶች ውስጥ የሰጠሙት ሁሉ በሚመሠክሩለት፥ ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ብዛት አልፎ በሚገኘው ምሕረትህ እማጸንሃለሁ። ስለዚህ በመከላከያህ ምሽግና በእንክብካቤህ መጠለያ ውስጥ ጠብቀኝ። አምላኬ ሆይ፥ እኔ፥ ብቸኛ ፍላጎቱ አንተ በኃያልነትህ ሥልጣን የወሰንከው የሆነው ነኝ። እኔ ለራሴ የመረጥኩት ጸጋ በተመላበት ትእዛዝህና በፈቃድህ ውሳኔ ለመደገፍ፥ በድንጋጌህና በፍርድህ ምልክቶችም እንድታገዝ ብቻ ነው።

አቤቱ፡ አንተ የእነዚያ አንተን የሚናፍቁት ልቦች ተወዳጅ የሆንከው ሆይ፥ ወደ አንተ ቅዱስ መንበር፥



ወደ አንተ ደጀሰላምና ወደ አንተ ቤተ-መቅደስ ከመቅረብ እንዳትነፍገኝ፡ በእምነትህ ክስተቶች፡ በዕውቀት--ብልጭታህም ንጋቶች፡ በግርማህም መገለጫዎች፥ በዕውቀትህም ግምጃ-ቤቶች እማጸንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፥ ወደ እርሱ ቅዱስ መንበር እንድደርስ፥ በእርሱም ስብዕና ዙሪያ እንድዞር፡ በእርሱም ደጃፍ ፊት በትሕትና እንድቆም እርዳኝ።

አንተ ሥልጣኑ ከእምቅድመ-ዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖረው ነህ። ምንም ነገር ከዕውቀትህ አያመልጥም። አንተ በእውነቱ፥ የሥልጣን አምላክ፥ የክብርና የጥበብ አምላክ ነህ።

የዓለማት ሁሉ ጌታ የሆነው፥ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

## 87

አቤቱ፡ አንተ አምላኬና የሁሉ ነገሮች አምላክ፡ ክብሬና የሁሉ ነገሮች ክብር፡ ፍላጎቴና የሁሉ ነገሮች ፍላጎት፥ ብርታቴና የሁሉ ነገሮች ብርታት፡ ንጉሤና የሁሉ ነገሮች ንጉሥ፡ ጌታዬና የሁሉ ነገሮች ባለቤት፡ ዓላማዬና የሁሉ ነገሮች ዓላማ፡ አንቀሳቃሼና የሁሉ ነገሮች አንቀሳቃሽ የሆንከው ጌታ ሆይ፡ ስምህ የተወደሰ ይሁን! ከፍቅራዊ ምሕረቶችህ ውቅያኖስ እንድከለከል፡ ክቅርበትህ ዳርቻዎችም እንድርቅ እንዳታደርገኝ እማጠንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ ከአንተ በቀር ሌላ ማንኛውም ነገር አይጠቅመኝም፡ ወደ አንተ በቀር ወደ ማንም መቅረቡም ምንም አይረዳኝም። ከእነዚያ ፊቶቻቸውን

ማቢህ ክልልም በመግባታቸው፡ እነዚህን ነፍሶች በጨካኝ አራዊት ጥፍሮችና ጥርሶች እንዲቦጫጨቁ አትተዋቸው።

ጌታ ሆይ! በጸጋህ፡ በአዲስ መንፈስ አጠናክራቸው፡ በሌሊት አስከፊ ጨለማ አስደናቂ ማስረጃዎችህን ለማየት እንዲችሉ ዓይኖቻቸውን አብራላቸው፡ በዘለዓለማዊ ምሥጢራት መንግሥትህ ውስጥ የተትረፈረፈውን መልካም ነገር ሁሉ አድላቸው። በመላው አካባቢ ላይ እንደሚያበሩ እንጸባራቂ ከዋክብት፡ ፍሬና ቅርንጫፍ አዝለው በጎሕ ልዝብ ነፋስ እንደሚወዛወዙ ዝርጋጋ ዛፎች አድርጋቸው።

በእውነቱ አንተ ጸጋ የተመላው፡ ኃያሉ፡ ምንም የማይሳነው፡ የማይገታው ነህና። ከአንተ፡ ከንዑዱ፡ ከዘላለም ቅር-ባዩ፡ የፍቅርና ርኅራኄ የተመላው ምሕረት አምላክ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

<u>ለይቅርታ</u>

85

"… ኃጢአትንና በደልን በሰዎች ፊት መናዘዝ… አይፈቀድም። … ኃጢአተኛው በራሱና በአምላክ መካከል እንዲህ በማለት ከምሕረት ውቅያኖስ ምሕረትን መማጸን፡ ከቸርነትም ሰማይ ይቅርታን መለመን አለበት፡ "

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ለእኔም ለአባቴም ለእናቴም ይቅር ባይነትህን ትፈቅድልን ዘንድ፡ በጣፋጭ ቃላትህ በጣም በመመስጣቸው የክብር ከፍታ ቁንጮ ወደሆነው፡ ወደ እጅግ በጣም ታላቅ



ስግዕትነት ሥፍራ በፍጥነት በገሥገሡት በእውነተኞች አፍቃሪዎችህ ደም እማልድሃለሁ፡ በዕውቀትህ ውስጥ ተሸፍነው በሚገኙት ምሥጢራትና በበረከትህ ውቅያኖስ ውስጥ በተቀመጡት ዕንቁዎችም እማጸንሃለሁ። ከእነዚያ ምሕረትን ከሚያሳዩት፡ አንተ በእውነቱ ከሁሉም በላይ መሐሪው ነህ። ከአንተ ከዘለዓለም ይቅር ባዩ፡ ፍጹም በረከት ከተመላው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ጌታ ሆይ! ይህ የኃጢአተኛነት ሕልውና ወደ ልግስናህ ውቅያኖስ ፊቱን ሲመልስ፡ ይህም ደካማው የመለኮታዊ ኃይልህን መንግሥት ሲሻ፡ ይህም ድሀው ፍጡር ራሱን ወደ ሀብትህ የቀኑ ኮከብ ሲያዘነብል ታየዋለህ። ጌታ ሆይ፡ በምሕረትህና በጸጋህ፡ እርሱ የለመነህን አትንሳው፡ ከበረከትህም ግልጸቶች አትከልክለው፡ በሰማይህ ውስጥና በምድርህ ላይ ለሚኖሩት ሁሉ በሰፈው ከከፈትከው በርህም አታብርረው።

እግዚአ ! እግዚአ! ኃጢአቶቼ ወደ ቅድስናህ መንበር ከመቅረብ ከልክለውኛል፡ በደሎቼም ከግርማ ሞገስህ ድንኳን በጣም ርቁ እንድጠፋ አድርገውኛል። አንተ እንዳላደርግ የከለከልከኝን አድርጌአለሁ፡ እንድፈጽመው ያዘዝከኝን አልፈጸምኩም።

ወደ አንተ ለመቅረብ የሚያስችለኝን በበረከትህ ብዕር ትጽፍልኝ ዘንድ በኔና በይቅርባይነትህ፡ በይቅርታህም መካከል ከተጋረጡት በደሎቼም ታነፃኝ ዘንድ፡ በእርሱ የስሞች ሉዓላዊ ጌታ በሆነው እለምንሃለሁ።

ወደ አንተ አቅጣጫ ከአቀኑትና፡ አንተን ለማገልገል ከተነሡት ጋር እንድትቆጥረኝ፡ ከአንተ ከራስህ በስተቀር ማንኛውም ነገር እንዳያስፈልግህ በአደረግህባቸው ሀብቶችህ ብዛት እማጠንሃለሁ።

እንግዲህ ፡ ጌታዬ ሆይ፡ ወንድ አገልጋዮችህንና ሴት አገልጋዮችህን ይቅር በላቸው። በእውነቱ፡ አንተ ምንጊዜም ይቅር ባዩ፡ ከሁሉም በላይ ሩኅሩኁ ነህና።

88

ጌታ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን። ኃጢአታችንን ይቅር በለን፡ በእኛ ላይ ምሕረት ይኑርህ፡ ወደ አንተም ለመመለስ አስችለን። በአንተ ላይ በቀር በሌላ በምንም ላይ እንዳንተማመን አድርገን፡በጸጋህ አማካይነት፡ ያንን አንተ የምትወደውንና የምትሻውን፡ ከአንተም በጣም የሚጠበቀውን ስጠን። የእነዚያን፡ በእውነት ያመኑትን ደረጃ ከፍ አድርግ፡ ጸጋ በተመላበት ይቅር-ባይነትህም ይቅር በላቸው። በእውነቱ፡ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፡ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህና።

89

ጌታዬ ሆይ፡ አቤቱ አንተ የጌቶች ጌታ፡ እርሱ ተፈላጊውን የሚሰጠውና በሮቹን ሁሉ የሚከፍተው የሆንከው ሆይ፡ የአንተን ስም ለማንሣት በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ስም ማንሣት፡ ለአንተ ውዳሴም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ውዳሴ፡ በቅርበትህ ምክንያት



ከተደሰትኩት ደስታም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ደስታ፥ ከአንተ ጋር በመቋረብ ምክንያት ለአገኘሁት እርካታም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ እርካታ፥ ለፍቅርህና ለመልካም ደስታህም ሐሴት በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ሐሴት፥ ከአንተ ጋር ምንም ግንኙነት ለሌላቸው፥ ከእኔ ጋር ግንኙነት ለነበራቸው ነገሮች ሁሉ ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ።

90

አቤቱ አንተ ፍጹም ኃያል አምላክ ሆይ! እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፥ አንተ ግን ይቅርባይ ነህ! እኔ ጥፋቴ የበዛ ነው፥ አንተ ግን ሩኅሩኅ ነህ፥ እኔ በስሕተቶች ጨለማ ውስጥ ነኝ፥ አንተ ግን የምሕረት ብርሃን ነህ !

አቤቱ አንተ ለጋሥ አምላክ ሆይ! ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፥ በረከትህን አውርድልኝ፥ ስሕተቴን አትመልከት፥ መጠለያ ስጠኝ፥ በትዕግሥትህ ምንጭ ውስጥ አስጥመኝ፥ ከማናቸውም ደዌና በሽታም ፈውሰኝ።

አንጻኝ፥ ቀድሰኝ፥ ኃዘንና ትካዜ እንዲጠፉ፥ ፍስሐና ሐሴት እንዲወርዱ፥ ከሚጎርፈው ቅድስናህ አካፍለኝ። ጭንቀትና ተስፋ ማጣት በደስታና በታማኝነት እንዲለወጡ አድርግልኝ፥ በፍርሐትም ፈንታ ልበ ሙሉነት እንዳገኝ ፈቃድህ ይሁን።

በእውነቱ አንተ ይቅር-ባዩ፥ ሩኅሩኁ፥ ለጋሱና ተወዳጁ ነህና።

91

አምላክ ሆይ! በጭካኔያቸው፡ በተሳሳተ ሥራቸውና በሚያደርጉት ተንኮል ሁሉ የዋሃን በመሆናቸው የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር ትላቸው ዘንድ በአፌም በልቤም እለምንሃለሁ:: ክፉውን ከደጉ፥ ስሕተቱን ከትክክለኛው፥ ፍትሕን ከፍርድ ማጓደል ለይተው ሳያውቁ የራሳቸውን ፍላጎት ያደርጋሉ፣ ከእነርሱ መካከል በጣም የተሳሳተውን ሰው ይከተላሉ:: አምላክ ሆይ፥ ምሕረትን አውርድላቸው፥ በዚህ በችግር ዘመን ከመከራ ሁሉ ጠብቃቸው:: ይህ ሁሉ መከራና ችግር ለዚህ በጨለማ ጉድጓድ ለተጣለው አገልጋይህ ይሆን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን:: ማናቸውንም ኃዘን ሁሉ ለእኔ አድርገው:: ለተወዳጆችህም ሁሉ መስዋዕት ለመሆን አብቃኝ፣ ለታላቅነትህ ወሰን የሌለው አምላክ ሆይ፥ ነፍሴ፥ ሕይወቴ፡ መላው ሰውነቴ፥ መንፈሴም ስለ እነርሱ መስዋዕት ይሆን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን:: አምላኬ ሆይ፡ የበደሉኝን፥ ያደሙብኝንና ፍርድንም ያጓደሉብኝን ሁሉ ይቅር እንድትላቸው ፥ እኔ ዝቅተኛው አገልጋይህ በግንባሬ ተደፍቼ እለምንሃለሁ:: መልካም ችሮታህን ናኛቸው፥ ደስታን ስጣቸው፥ ከኃዘን አድነህ ሰላምንና ብልጽግናን አድላቸው፥ ታላቅ ደስታን ስጣቸው:: በረከትህንም አውርድላቸው:: አንተ ራሱን ችሎ ነዋሪው፥ ኃያሉ፥ በአደጋ ጊዜም ረዳቱ ነህና::



ለውዳሴና ለምስጋና::

92

አምላኬ ሆይ፥ የክብርና የግርማ፥ የታላቅነትና የክቡርነት፥ የሉዓላዊነትና የገገርነት፥ የልዕልናና የጺጋ፥ የመከበርና የሥለጣን ሁሉ ምንጭ ለሆንከው ለአንተ ብቻ ምስጋና ሁሉ ይድረስህ:: አንተ የምትፈቅደውን ሁሉ ወደ እጅግ በጣም ታላቁ ውቅያኖስ እንዲቀርብ ታደርገዋለህ፥የመትወደውንም ሁሉ ዘለዓለማዊ ስምህን የማወቅን ክብር ታጎናጽፈዋለህ:: በሰማያትና በምድር ካሉት ሁሉ የከፍተኛ ፈቃድህን ፍጻሜ ሊያስቀር የሚችል ከቶ አይገኝም:: ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ ፍጥረትን ሁሉ ገዝተሃል፥ እስከ ዘለዓለምም በፍጡራን ሁሉ ላይ ገዥነትህ ከቶ አያቋርጥም:: ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፥ ከሁሉም በላይ ከተከበረው፥ ፍጹም ኃይል ከተመላው፥ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ አገልጋዮችህ አንተን ለማየት ይችሉ ዘንድ ፊቶቻቸውን አብሪላቸው፥ ወደ መንግሥተ ሰማያዊ ችሮታዎችህ መንበር እንዲዞሩ፥ እርሱን የአንተ የራስህ ክስተትና የህላዌህ ጎሕ የሆነውን እንዲያውቁ ልቦቻቸውን አንፃ:: በእውነቱ አንተ የዓለማት ሁሉ ጌታ ነህና:: ከአንተ ጨቋኝ ከሌለበትና ሁሉን ድል ከሚነሣው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::

የተመሰገንክና የተወደስክ ነህ ፥ ጌታ አምላኬ ሆይ! ምንም ያህል ጥበቡ የጠለቀ አንደበት ስምህን በተገቢ ሁኔታ ለማወደስ እንደማይችል፥ የሰው ልብ ወፍም ፥ ምንም ያህል ታላቅ ናፍቆትና ፍላጎት ቢኖረውም ፥ ወደ ግርማህና ወደ ዕውቀትህ ሰማይ ሊያርግ እንደማይችል እያወቅሁ ፥ እንዴት ስምህን ላነሳ እችላለሁ፡፡

አምላኬ ሆይ! ሁሉን የሚያስተውል ብዬ ብገልጽህ፥ እነዚያ ፍጹም ከፍተኞቹ የማስተዋል ክስተቶች በአንተ ትእዛዝ መፈጠራቸውን እንድቀበል እገደዳለሁ፡፡ ፍጹም ጠቢቡ ብዬ ባወድስህም፥ እንደገና የጥበብ ምንጮች የሆኑት ራሳቸው በአንተ ፈቃድ መፍለቃቸውን እንዳውቅ እገደዳለሁ፡፡ ተወዳዳሪ የሌለው ብዬ ብገልጽህም፥ እነዚያ የአንድነት ውስጣዊ ህልውና የሆኑት በአንተ ወደዚህ የተላኩና የአንተ የእጅ ጥበብ ማረጋገጫዎች መሆናቸውን ወዲያውኑ እረዳለሁ፡፡ ሁሉን ነገሮች አዋቂው ብዬ ብጠራህም ፡ እነዚያ የዕውቀት የመጨረሻ ከፍተኛ ህልውና የሆኑት የዓላማህ ፍጥረቶችና መሣሪያዎች መሆናቸውን ማመን አለብኝ፡፡

የሚች ሰው ጥረት ምሥጢርህን ለመፍታት፥ ክብርህን ለመግለጽ ፥ የሕላዌህን ባሕርይ እንኳ ለመጠቆም ከሚችለው በላይ የተከበርክ ፥ ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ፡፡ እነዚህ ጥረቶች በትእዛዝህ የተንቀሳቀሱና የአንተ ፈጠራ ውጤቶች በመሆናቸው ፥ እንዲህ ያሉት ጥረቶች ምንም ዓይነት



ውጤት ቢያስገኙም ፡ ለፍጡራንህ ከወሰንከው ገደብ የማለፍ ተስፋ ሊኖራቸው ከቶ አይችሉም፡፡ እጅግ በጣም ብፁዕ የሆኑት ቅዱሳን አንተን ለማወደስ የሚያቀርቡት ከፍተኛ ስሜት፡ እጅግ በጣም የተማሩት ሰዎች የአንተን ባሕርይ ለመረዳት በመሞከር ሊናገሩት የሚችሉት እጅግ በጣም ጥልቅ ጥበብ፡ በዚያ በአንተ ሉዓላዊነት ሙሉ በሙሉ በሚገዛው፡ የአንተን ውበት በሚያስጌጠው፥ በአንተ ብዕር ኃይል በሚንቀሳቀሰው ማዕከል ዙሪያ ይሽከረከራሉ፡፡

አምላኬ ሆይ ! በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ሕልውናና በግልጸትህ ብዕር መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለ የግድ የሚያመለክቱትን ዓይነት ቃላት ስለመናገሬ ይቅር በለኝ፡፡ እነዚያ ከአንተ ጋር ግንኙነት ያላቸው ፥ ከዚህ ዓይነቱ የማዛመድ ሃሣብ በላይ በጣም፥ በጣም ከፍ ያሉ ናቸው፡፡ ማንኛውም ማወዳደርና ማመሳሰል ለግልጸትህ ዛፍ ተገቢ አይደለም፥ የአንተን ክስተትና የውበትህን ጎሕ የመረዳት መንገድ ሁሉ ተዘግቷል፡፡

ሚች ሰው ስለ አንተ ሊናገር ወይም አንተን ሊገልጽበት የሚችለው ባሕርይ ወይም አንተን ሊያወድስበት የሚችለው ምስጋና ከአንተ ክብር በጣም የራቀ ይሁን! አገልጋዮችህን ያዘዝካቸው ፡ የተቻላቸውን ያህል ግርማህንና ክብርህን የማወደስ ማንኛውም ምግባር ፡ ለራሳቸው እጅግ ጥልቅ ሕያውነት ወደ ተሰጠው ደረጃ፡ ራሳቸውን ወደ ማወቅ ደረጃ ለመድረስ የሚያስችላቸው የአንተ ጸጋ ምልክት ብቻ ነው፡፡

በምንም ጊዜ ፡ ከአንተ በስተቀር የአንተን ምሥጢር ጠልቆ ለማወቅ፥ ወይም የአንተን ታላቅነት በሚገባ ለማወደስ የቻለ የለም ። አንተ በምርምር የማትገኝ ፡ ከሰዎችም ምስጋና በላይ ሆነህ ዘለዓለም ትኖራለህ ። የማይደረስብህ ፥ ምንም የማይሳንህ፥ ሁሉን አዋቂ ፡ የቅዱሳን ቅዱስ ከሆንከው ከአንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።



አምላኬ ሆይ፡ የክብሮች ክብርና ከሁሉ በላይ እንጸባራቂው ብርሃን በአንተ ላይ ይረፍ። ግርማህ በጣም የመጠቀ በመሆኑ ምንም የሰው ሃሳብ ሊደርስበት አይችልም፥ ፍጹም ኃይልህም በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፥ የሰዎች ልቦችና አዕምሮዎች አእዋፋት ከፍታዎቹ ላይ ለመድረስ ከቶ አይችሉም። ሕያዋን ሁሉ ለደረጃህ እንደሚገባ ሊያወድሱህ ኃይል አልባነታቸውን ይገልጻሉ። ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ። አንተ በራስህ እንዳለህ የምታውቀው ራስህ ብቻ ስለሆንክ ሕያውነትህን ሊያሞግስ፥ ወይም ከሁሉም በላይ ጥልቅ በሆነው ውሳጣዊ ህልውናህ በሚገኘው ሁኔታ የበረከትህን ማስረጃዎች ጠልቆ ለመረዳት የሚችል ማንም የለም።

ጌታ አምላካችን ሆይ፥ የፍጥረትንና የፈጠራን ዓለም ወደ መኖር ለጠራህበት በረከት፡- ከአንተ በቀር ሌላ ማንም በሚገባ ሊገምተው በማይችለው፥ በማንቀቂያህ ኃይል በድምቀት በሚያበራው ምስጋና፥ ለአንተ ምስጋና አቀርባለሁ። ከዚህም በላይ፥ ለዚህ



ቅዱስ ቡራኬ፥ ለዚህ በግልጸትና በፍጥረት መንግሥቶችህ ለተገለጸው ድንቅ ምልክት፥ ለአስፈሪ ቅርበትህና ለአሸናፊው ግርማህ ክብር እንደሚገባው አወድስሃለሁ፥ ምስገናም አቀርብልሃለሁ።

ክብር ሁሉ ለአንተ ይሁን። ያ ለአንተ የሚገባው ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበረ ነው። በእውነቱ የደረጃህን ምጥቀት ማንም በቂ በሆነ ሁኔታ ተረድቶት፥ ወይም ከአንተ በቀር ሌላ ማንም ለአንተ እንደሚገባ አውቆህ አያውቅም። ከአንተ በቀር ሌላ የግልጸትህን ከፍተኝነት ለመገመት የሚችል የሌለ ሲሆን፥ አንተ በሰፊ በረከትህ ጎርፎች አማካይነት ትገለጻለህ።

ስምህ የተወደሰ ይሁን። ከአንተ በቀር ሌላ ማንም የባሕርይህን ፍንጭ እንኳ ለመናገር ይችል ዘንድ ነፃ ህልውና አለውን? ከአንተም በቀር ሌላው አንተን ሳውቅበት የምችልበት የአምሳል ምልክት አለውን? የታወቀ ሁሉ መታወቁን የሚያገኘው፥ ከሁሉም በላይ ግልጹ ከሚለው ስምህ ውበት ነው፤ እያንዳንዱ ነገር ከማይሸነፈው ፈቃድህ በሚፈልቀው አርገብጋቢ ኃይል ከሥረ መሠረቱ ተንቀሳቅሷል። አንተ ከሁሉም ነገሮች ይበልጥ ለሁሉ ነገሮች ቅርብ ነህ።

የተመሰገንክና የተከበርክ ነህ። ምጥቀትህ እነዚያ የመረዳት ኃይልን የተለገሱት ሰዎች እጆች ወደ አንተ ለመዘርጋት ከሚችሉበት ከፍታ የላቀ ነው፤ መጨረሻ የሌለውም ጥልቀትህ የሰዎች አዕምሮዎችና የመገንዘብ ችሎታዎች ወንዞች ከዚያ ለመጉረፍ ከሚችሉበት ይበልጥ ጥልቅ ነው።

95

አቤቱ፡ አንተ ሩኅሩኅ ጌታ ሆይ! አንተ ለጋሱና መሐሪው ሆይ! እኛ የደጀሰላምህ አገልጋዮች ነን፡ በከለላ ሰጪውም የመለኮታዊ አንድነትህ ጥላ ሥር ተሰብስበናል። የምሕረትህ ፀሐይ በሁሉም ላይ ያበራል፡ የበረከትህም ደመናዎች በሁሉም ላይ ያዘንባሉ። ስጦታዎችህ ሁሉንም ይከባሉ፡ ፍቅራዊ አምላካዊ ጥበቃህ ሁሉን በሕይወት ያኖራል፡ የአንተ ጥበቃ ሁሉን ይከልላል፡ የችሮታህ እይታዎችም በሁሉም ላይ ያርፋሉ። ጌታ ሆይ! የማያልቁትን ስጦታዎችህን ስጠን ፡ የመርሖህም ብርሃን እንዲያበራ ፈቃድህ ይሁን። ዓይኖችን አብራ፡ ልቦችን በማያቋርጥ ሐሴት አስደስት። በሁሉም ሰዎች ላይ አዲስ መንፈስ ዝራ፡ ዘላለማዊ ሕይወትንም አጎናጽፋቸው። የእውነተኛ ማስተዋልንም በሮች ክፈት፡ የእምነትም ብርሃን በድምቀት እንዲያበራ ፈቃድህ ይሁን። ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ፀሐይ ጨረሮች፡ እንደ አንድ ውቅያኖስ ማዕበሎች፡ እንደ አንድ ዛፍም ፍሬዎች ይሆኑ ዘንድ፡ በቸርነትህ ጥላ ሥር ሰብስባቸው፡ እንዲስማሙና አንድ እንዲሆኑም አድርጋቸው። ከአንድ ምንጭ እንዲጠጡ ይሁን፡ በአንድ ልዝብ ነፋስም እንዲነቃቁ ፈቃድህ ይሁን። ከአንድ የብርሃን ምንጭም ብርሃን ይቀበሉ። አንተ ሰጪው፡ መሐሪው፡ ምንም የማይሳነው ነህና ።



ለእርዳታ።

96

አቤቱ፡ አምላኬ፡ ተወዳጄ፡ ንጉሤ፡ ፍላጎቴ ሆይ! ለአንተ የማቀርባቸውን ምስጋናዎቼን ምን እንደበት ሊያወሳቸው ይችላል? ደንታ-ቢስ ነበርኩ፡ ቀሰቀስከኝ። ከአንተ ዞሬ ነበርኩ፡ ወደ አንተ እንድመልስ በጸጋህ ረዳኸኝ። እንደሞተ ሰው ነበርኩ፡ በሕይወት ውሀ ነፍስ ዘራህብኝ። ጠውልጌ ነበርኩ፡ አንተ ከፍጹም መሐሪው ብዕር በኀረፋት የቃላትህ መንግሥተ-ሰማያዊ ጅረት ሕይወት ዘራህብኝ።

መለኮታዊው ጠባቂ ሆይ! መላው ኑባሬ በጸጋህ የተገኘ ነው፡ ከቸርነትህ ውሀዎች አትንፈገው፡ ከምሕረትህም ውቅያኖስ አትከልክለው። በሁሉ ጊዜያትና በሁሉ ሁኔታዎች እንድትረዳኝና እንድትደግፈኝ፡ ጥንታዊ ቸርነትህንም ከጸጋህ መንግሥተ-ሰማይ እንድፈልግ እንድታደርገኝ እማጸንሃለሁ። በእውነቱ፡ አንተ የጸጋ ጌታ፡ የዘለዓለማዊ መንግሥት ንጉሥ ነህና።

97

ጌታ ሆይ፡ አንተ የተከበርክ፡ ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ! ጠልቆ የመረዳት ችሎታ ያለው እያንዳንዱ ሰው አንተን አውቆ ለመቀበል በሚያደርገው ሙከራው በጣም መንገድ ስቷል፡ እያንዳንዱም የበቃ የዕውቀት ሰው ስለ አንተ

በሚያደርገው ምርምር ከፉኛ ግራ ተጋብቷል። እያንዳንዱ ማስረጃ ሊታወቅ ወደማይቻለው የአንተ ሕላዌ ለመድረስ አይችልም፡ እያንዳንዱም ብርሃን ከኀያልነትህ የሚያፈዝ ነጸብራቅ ውስጥ ከጭላንጭሉ ብቻ ጋር እንኳ ቢወዳደር ወደኋላ ያፈገፍግና ከአድማስ በታች ይጠልቃል።

ጌታዬ ሆይ፡ ጸጋ የተመላበት በረከትህንና በጎ ስጦታዎችህን አጎናጽፈኝ፡ ከክብርህ ከፍተኛነት ተገቢ የሆነውንም ፍቀድልኝ። ጌታዬ ሆይ፡ ልዩ ድል ለማግኘት እንድችል እርዳኝ። የማይቀር የዓላማ ስኬት በር በፊቴ ክፈትልኝ፡ አንተ ቃል የገባሃቸው ነገሮች በቅርብ ጊዜ እንዲደርሱ ፈቃድህ ይሁን። አንተ በእውነቱ በሁሉ ነገሮች ላይ ኀይል አለህ። አምላኬ ሆይ፡ ልቤን በፍቅርህ የሕይወት ውሀዎች አድስልኝ፡ ጌታዬ ሆይ፡ከለጋ ምሕረትህ ጽዋ አርኪ መጠጥ ስጠኝ። ጌታዬ ሆይ፡ በክብርህ መኖሪያ ውስጥ እንድኖር ፍቀድልኝ፡ አምላኬ ሆይ፡ መለኮታዊ ሥውርነትህ ከተሸፈነበት ጨለማ ውስጥ እንድወጣ አድርገኝ። ለእርሱ፡ ንቁጥ ለሆነውና ለእነዚያ የእርሱ እምነት ደጋፊዎች ለሆኑት ከሰጠኸው ከእያንዳንዱ መልካም ነገር ለመካፈል አስችለኝ፡ ከአንተ መሰጠቱ የሚጠበቀውንና ለደረጃህ የሚገባውን እዘዝልኝ። በቅዱስ ቅርበትህ ለፈጸምኋቸው ክፉ ነገሮች በጸጋህ ይቅር በለኝ፡ በጸጋህ አድነኝ እንጂ፡ በፍትሕ አይታ አትመልከተኝ፡ ለክብርህ በሚገባው ሁኔታ፡ በምሕረትህ አያያዝ ያዘኝ፡ በረከት ለተመላባቸው ችሮታዎችህም የሚመጥነውን ለግሰኝ።



አንተ ዘለዓለም ይቅርባዩ፡ ንሁዱ ፡ ችሮታዎችንና ሥጦታዎችን አጎናጻፊው፡ ወሰን የሌለው ጸጋ ጌታ ነህና። በእውነቱ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም። አንተ ሁሉ ያለው፡ ከሁሉም በላይ ከፍተኛው ነህ።

98

እግዚአብሔር ጌታችን ሆይ! ለአንተ ከሚያስጸይፈው ከማንኛውም ነገር በጸጋህ ጠብቀን፡ ከአንተ መሰጠቱ ተገቢ የሆነውን ስጠን። ከሰፊ ቸርነትህ ጨምርልን፡ እንዲሁም ባርከን። ለፈጸምናቸው በደሎች ይቅርታ አድርግልን፡ ኀጢአቶቻችንንም ከላያችን እጠብልን፡ ጸጋ በተመላበት ይቅር ባይነትህም ይቅር በለን። በእውነቱ አንተ ከሁሉም በላይ የተከበረው፡ ቢጋዛ ራሱም ነዋሪው ነህና።

ፍቅር የተመላበት አምላካዊ ጠባቂነትህ፡ በሰማዮትና በምድር የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ አትሯል፡ ይቅር ባይነትህም ከመላው ፍጥረት አልፎ ተርፏል። ሉዓላዊነት ያንተ ነው፡ የፍጥረትና የግልጸት ዓለማት በእጅህ ናቸው፡ በቀኝ እጅህ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ይዘሃል፡ የይቅር ባይነትህ የተመደቡ መጠኖች በመዳፍህ ውስጥ ናቸው። ከአገልጋዮችህ መካከል ለፈለግኸው ለማንኛውም ይቅር ትለዋለህ። በእውነቱ አንተ ዘለዓለም ይቅር ባዩ፡ ሁሉን አፍቃሪው ነህ። ምንም ነገር ማንኛውም ቢሆን፡ ከዕውቀትህ አይመልጥም፡ ከአንተ የተሰወረ ምንም ነገር የለም።

እግዚአብሔር ጌታችን ሆይ! በኃያልነትህ ኃይል ጠብቀን፡ በመትመም ላይ ወዳለው ድንቅ ውቅያኖስህ ለመግባት አስችለን፡ ከአንተ መፈቀዱ ተገቢ የሆነውን ፍቀድልን።

አንተ የላቀው ገዢ፡ ኃያሉ አድራጊ፡ የተከበረው፡ ሁሉን አፍቃሪው ነህና።

99

ጌታ ሆይ! ምስኪኖች ነንና ችሮታህን ስጠን ፡ ድሆች ነንና ከሀብትህ ውቅያኖስ አጋራን፣ ችግረኞች ነንና አጥግበን፣ የተዋረድን ነንና ክብርህን አጎናጽፈን። የሰማይ አዕዋፋትና የየብስ እንስሶች ሁሉ ምግባቸውን በየቀኑ ከአንተ ያገኛሉ። ሕያዋንም ሁሉ ከአንተ ጠባቂነትና ፍቅራዊ ደግነት ይካፈላሉ።

ይህን ደካማ ፍጡር ግሩም ጸጋህን አትንሣው፡ በኃያልነትህም ለዚህ ምስኪን ነፍስ ቸርነትህን ስጠው።

የዕለት እንጀራችንን ስጠን፣ የአንተ እንጂ የሌላ ጥገኞች እንዳንሆን፡ ከአንተም ጋር በፍጹም እንድንቋረብ፡ በአንተም መንገድ እንድንመላለስና ምሥጢርህን ለመግለጽ እንድንችል ለሕይወት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ መጠን አብዛ። አንተ ፍጹም ኃያሉ፡ አፍቃሪውና ለሰው ዘር ሁሉ አስፈላጊውን ሰጪው ነህና።

100

ጌታ ሆይ! ደካሞች ነንና አበርታን። አምላክ ሆይ! ዕውቀተ ቢስ ነንና አዋቂዎች አድርገን። ጌታ



ሆይ! ድሆች ነንና ባለጸጋዎች አድርገን። አምላክ ሆይ! የሞትን ነንና የሕይወት እስትንፋስ ዝራብን። ጌታ ሆይ! ውርደት ራቧን ነንና በመንግሥትህ ውስጥ ክብርን አጎናጽፈን። ጌታ ሆይ፡ አንተ ከረዳኸን እንደሚያበሩት ከዋክብት እንሆናለን። አንተ ካልረዳኸን ግን ከአፈር በታች እንሆናለን። ጌታ ሆይ! አበርታን። አምላክ ሆይ! ድልን አጎናጽፈን። አምላክ ሆይ! እኔነትን ለማሸነፍና ከከንቱ ምኞት በላይ ለመሆን አስችለን። ጌታ ሆይ! ከዓለማዊ ቁራኛነት አድነን። ጌታ ሆይ! አንተን ለማገልገል እንድንነሣሣ፡ ለአንተ መስገድ ተግባራችን፡ በመንግሥትህም ውስጥ ተሳትፎአችን በሙሉ ልብ እንዲሆን በቅዱስ መንፈስ እስትንፋስ አንቃን። ጌታ ሆይ! አንተ ኃይል የተመላው ነህ! አምላክ ሆይ፡ አንተ ይቅር-ባዩ ነህ! ጌታ ሆይ፡ አንተ ሩኅሩኅ ነህ!

ለአንድነት።

101

አምላኬ ሆይ! አምላኬ ሆይ! የአገልጋዮችህን ልብ አስተባብር፡ ታላቁን ዓላማህንም ግለጽላቸው። ትእዛዝህን ይከተሉ፡ በሕግህም ይኖሩ ዘንድ ፡ አምላክ ሆይ፡ በጥረታቸው እርዳቸው፡ ለአንተም እንዲያገለግሉ ኃይልን ስጣቸው። አምላክ ሆይ! ራሳቸውን ለራሳቸው አትተው፡ እርምጃቸውን ሁሉ በዕውቀት ብርሃን ምራው፡ በፍቅርህም ልቦቻቸውን አስደስት። በእውነቱ፡ አንተ ረዳታቸውና ጌታቸው ነህና።

102

የአንድነት ብርሃን መላዋን ⁽¹⁾ ዓለም እንዲያለብስና፥ "መንግሥት የአምላክ ናት" የሚለውም ማኅተም በሕዝቦቿ ሁሉ ግንባር ላይ እንዲታተም የአምላክ ፈቃድ ይሁን።

103

አምላኬ ሆይ! አምላኬ ሆይ! በእውነቱ፡ ምሕረቶችህ ሁሉ በእነዚህ ነፍሶች ላይ እንዲወርዱ አንተን በመጠየቅ እለምንሃለሁ፡ በደጅ-ሰላምህ ፊት ሆኜ እማጸንሃለሁ። ለችሮታህና ለእውነትህ ምረጣቸው።

ጌታ ሆይ! ልቦችን በማስተባበር አስተሳስራቸው፡ ነፍሶችን ሁሉ በስምምነት አጣምራቸው፥ መንፈሶችንም በቅዱስነትህና በአንድነትህ ምልክቶች አስደስታቸው። ጌታ ሆይ! እነዚህን ፊቶች በአንድነት ብርሃን አማካይነት ብሩህ አድርጋቸው። ለመንግሥትህ እንዲያገለግሉ የአገልጋዮችህን ሽንጦች አጠንክርላቸው።

አቤቱ፡ አንተ ወሰን የሌለው ምሕረት ባለቤት የሆንከው ጌታ ሆይ! አቤቱ፡ የኃጢአት ስርየትና የይቅርታ ጌታ ሆይ! ኃጢአቶቻችንን አስተሰርይልን፥ ስለጉድለቶቻችንም ይቅርታ አድርግልን፡ ወደ ኃያልነትና ወደ ሥልጣን መንግሥት በመጸለይ፥ በመንበርህ ቅርበት ትሑታን፡ በማስረጃዎችህም ክብር ፊት ታዛገሮች በመሆን ወደ ምሕረትህ መንግሥት ፊቶቻችንን እንድንመልስ አድርገን።



አቤቱ፡ ጌታ አምላክ ሆይ! በፍቅርህ በረከት እንደ ባሕር ማዕበሎች፡ እንደ አትክልት ሥፍራ አበቦች የተባበርንና የተስማማን እንድንሆን አድርገን። ጌታ ሆይ! በአንድነትህ ምልክቶች አማካይነት ልቦችን አስፋቸው፥የሰው ዘርንም ሁሉ ከአንድ ዓይነት የክብር ከፍታ እንደሚያበሩ ከዋክብት፥ በሕይወት ዛፍህ ላይ እንደሚያድጉ ፍጹማን ፍሬዎች አድርጋቸው።

በእውነቱ፡ አንተ ፍጹም ኃያሉ፡ በገዛ ራሱ ነዋሪው፥ ሰጪው፥ ይቅር ባዩ፡ መሐሪው ፥ሁሉን አዋቂው፥ አንድዬው ፈጣሪ ነህና።

## ከዓለማዊ ቁራኛነት ለመላቀቅ

104

አምላኬ ሆይ፥ አንተ የተወደስክ ነህ! እርሱን የምሕረትህ ጎሕ፥ የጸጋህ የንጋት ሥፍራ፥ የእምነትህም ማኅደር የሆነውን እንዳውቅ ስለአደረግኸኝ ለአንተ ምስጋና አቀርባለሁ። በሁሉ ጊዜያትና በማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ ሆኜ የአንተን ገመድ አጥብቄ እንድይዝ፥ ከአንተም በስተቀር ከሌላ ከማንኛውም ሰው ጋር መቆራኘትን ሁሉ እንዳስወግድ፡ ዓይኖቼን በግልጸትህ አድማስ ላይ እንዳተኩር፡ በመልእክቶችህ ውስጥ አንተ ያዘዝከኝን ሁሉ እንድፈጽም እንድትፈቅድልኝ፡ ለአንተ የቀረቡት ሰዎች ገጽታዎች በበሩበት፡ ለአንተ ያደሩት ሰዎች ልቦች ወደ አንተ በረሩቸውን በአደረጉበት ስምህ እማጸንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፥ ውስጣዊውንም ውጫዊውንም ሰውነቴን በቸሮታዎችህና በፍቅራዊ ደግነትህ ልብስ አልብስልኝ። ለአንተ በሚያስጠላው በማንኛውም ነገር ከመበከልም ጠብቀኝ፤ እኔና ዘመዶቼም አንተን እንድንታዘዝ በጸጋህ እርዳን፡ እኔም ማንኛውንም የክፋት ወይም የርኩሰት ፍላጎት በውስጤ ከሚቀሰቅስ ነገር ሁሉ እንድርቅ እርዳኝ።

አንተ በእውነቱ፥ የመጣው የሰው ዘር ጌታ፡ የዚህ ዓለምና የሚቀጥለው ዓለም ባለቤት ነህና። ከአንተ ከሁሉን አዋቂው፥ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

105

አምላኬ ሆይ፡ ስምህ የተወደሰ ይሁን! አቤቱ አንተ የመጣው የሰው ዘር ጌታ ሆይ፡ በፍቅሬ ስሜቶች ሁሉ ወደ አንተ ለመመለስ እችል ዘንድ፡ከእውነት የራቁ እምነቶችንና ከንቱ አስተሳሰቦችን ሁሉ ከልቤ ውስጥ እንድታነጻልኝ፡ በአንተ ትእዛዝና የአንተን ፈቃድ በመከተል በመጣው ፍጥረት ውስጥ በተገኙት በጸጋህ ልብስ መዓዛዎች፡ በኃያልነትህና በሉዓላዊነትህ ኃይል አማካይነት፡ ከምሕረትህ አድማስ በላይ በአንጸባራቂነት በአበራው በፈቃድህ የቀኑ ኮከብ እማጸንሃለሁ።

አምላኬ ሆይ፡ እኔ አገልጋይህ የአገልጋይህም ልጅ ነኝ! እኔ የጸጋህን እጀታ አጥብቄ ይዣለሁ፡ ፍቅር በተመላበት ምሕረትህ ገመድም ላይ ተንጠላጥያለሁ። ከአንተ ዘንድ የሚገኙትን መልካም ነገሮች እዘዝልኝ፡



ከቸርነትህ ደማናዎችና ከቸሮታህ መንግሥተ ሰማይ ከላከኸው ገበታም መግበኝ።

አንተ በእውነቱ፡ የዓለማት ጌታ፡ በመንግሥተ ሰማይ የሚገኙት ሁሉ፡ በምድር ላይ የሚገኙትም ሁሉ አምላክ ነህና።

106

አምላኬ ሆይ፡ በምድርህ ውስጥ ያቀጣጠልከው ምን ዓይነት እሳት እንደሆነ አላውቅም። ድምቀቱን አፈሩ ሊያደበዝዘው ከቶ አይችልም። ነበልባሉንም ውሀ ሊያጠፋው አይችልም። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ኃይሉን ለመቋቋም ኃይል አልባ ናቸው። ወደዚህ እሳት የቀረበ፡ የጩኸቱንም ድምጽ የሰማ ቡሩኬው ታላቅ ነው።

አምላኬ ሆይ፡ አንዳንዶቹን በሚያጠናክረው ጸጋህ አማካይነት ወደዚያ እሳት ለመቅረብ አስቻልካቸው፡ ሌሎቹን ግን በቀናትህ እጆቻቸው በሠሯቸው ክፉ ሥራዎች ምክንያት ከዚያ ከለከልካቸው። ወደዚያ በፍጥነት የገሰገሰና እዚያ የደረሰ ማንኛውም ሰው፡ በውበትህ ላይ ለማተኮር ባለው ጉጉት፡ በመንገድህ ሕይወቱን ሰጠ፡ ከአንተ ከራስህም በስተቀር ከሌላ ከማንኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ በመላቀቅ ወደ አንተ አረገ።

ጌታዬ ሆይ፡ በግርማህ ዙፋን ፊት ከመቅረብ፡ በበርህም ደጃፍ ላይ ከመቆም የከለከሉኝን ግርዶሾች እንድትቀድልኝ፡ በዚህ በፍጥረት ዓለም በሚነደውና በሚንቀለቀለው እሳት እማጸንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፡